ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፤ አንድምታቸው እና የሚያስከትሉት የህግ ተጠያቂነት



ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

የማሕበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

አብርሃ መሠለ ዝናቡ (ኤል ኤል ቢ፣ ኤል ኤል ኤም፣ሌክቸረር፣ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ህግ ትምህርት ቤት)

የኢሜል አድራሻ፡ expansion97@gmail.com

ስልክ ቁጥር፡ +251920259716

ሕዳር 2007 ዓ.ም

የስልጠናው አላማዎች

❖ዋና አላማ

- የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተለያዩ አገራዊ እና አለም አቀፋዊ ህጎች ያላቸውን ክልከላ እና የሚያስከትሉትን የህግ ተጠያቂነት ለስልጣኞች በማብራራት ሕብረተሰባዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት::

❖ንኡሳን አላማዎች

- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚያስከተሉትን የተለያዩ የሕግ ተጠያቂነት ረገድ ላይ የሕብረተሰቡን የግንዛቤ ክፍተት መሙላት፤
- ጋብቻ እና ቤተሰብ የሚደረግላቸው ጥበቃ በጋራ ለመስራትና ሕብረተሰቡም ከዚህ ጥበቃ ተጠቃሚ በሚሆንበትን ንድፈ-ሃሳብ ላይ መወያየት፤
- በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ የተቀናጀ እና ሁሉን አቀፍ ስራ ለመስራት፤
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ እና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተለያዩ ህጎች ላይ ያላቸው ክልከላ እና የሚያስከተሉትን ተጠያቂነት ለሕብረተሰቡ ማሳወቅ::

ይዘቶች

- ❖የባህል ምንነትና ያለው ህገ-መንግስታዊ እውቅና
  - ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
  - ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?
  - ህገ-መንግስታዊ ክልከላና እውቅና
- ❖የህፃናት ጥበቃና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች
  - ህፃናት የትኞቹ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው?
    - የህፃን ትርጉም
- ❖የህፃናት ጥበቃ በተለያዩ ህጎች
- ❖ህፃናት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ
- ❖ያለ ዕድሜ ጋብቻ በህፃናት ላይ የሚያስከትለው ውጤት
  - በትምህርታቸው
  - በጤንነታቸው(በአካላቸው ፣ በስነ አእምሮአቸው እና በህይወታቸው)
  - ከህብረተሰባዊ ተሳትፎ መገለልን(social stigma and absence of participation)

- በሰብዓዊ ክብራቸው

❖ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ እይታ

❖የማህበረሰቡ ግዴታዎችና ተጠያቂነት

❖የመንግስት ግዴታችና ተጠያቂነት

አጠቃላይ መግቢያ

አንድ ማሕበረሰብ ከሚለካባቸው መመዘኛዎች ዋነኛው ጉዳይ ለአባላቱ ክብርና ደህንነት የሚሠጠው ዋጋና ይህንንም እሴት ተግባራዊ የሚያደርግበት መጠን ነው።።

አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ፌዴራላዊ ስርዓት በህገ-መንግስቱ በማካተት የብሔር ፡ ብሔረሰቦች ፡ ሕዝቦች የማንነት መገለጫ የሆኑትን ባህሎች ያለ ምንም ገደብ የማሳደግ ባህሉን የመግለፅ፡የማዳበርና የማስፋፋት መብት እንደተሰጠው በአንቀፅ 39 ንኡስ 2 ፣ አንቀፅ 34(4 እና 5) እና 78(5) እንዲሁም በህገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ አስፍሮ ይገኛል።። ይህም ብዝሃነትን እውቅና በመስጠት የጋራ ጠቃሚ እሴቶች የሆኑትን ማዳበርና አብሮ ለመኖርና እኩል ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ መሆኑ ይታመናል።።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ ህገ-መንግስቱ በተለያዩ አንቀፆች ክልከላ ያደረገባቸው ናቸው።። ከዚህም ባለፈ በአለም አቀፍ ህጎች የተካተቱ ጠቃሚ እሴቶችን የሚጥሱ ድርጊቶች ናቸው።። ለምሳሌ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በአንቀፅ 35(4) እና 9(1) እና ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 7

ከህገ-መንግስቱ በተጨማሪ በተለያዩ ህጎች ጎጂ ያልሆኑት ልማዳዊ ባህሎችን እወቅና የሚሰጡ፤ ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ደግሞ የሚከለክሉና

ቅጣት የሚጥሉ አሉ፡፡ ለምሳሌ በቤተሰብ ህጎች(በፌዴራላዊ ስርዓት ምክንያት)፡- በኢፌዴሪ ወንጀል ህጉ እና ሌሎች ህጎች ተሰባጥረው ይገኛሉ፡፡

ኢትዮÉያ ከኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የዓለም አቀፍ ሰነዶች እና የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ መግለጫዎች ተቀብላ ያፀደቀችና በሕገ-መንግስ~ በተለያዩ አንቀፆች ያካተተች ሃገር ናት ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፡፡

- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ እ. ኤ.አ 1948 ይፋ የተደረገ
- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢኮኖሚ፣ ማሕበራዊና የባህል መብቶች ስምምነት እ. ኤ.አ በ1976 የፀደቀ
- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት እ. ኤ.አ 1976 የፀደቀ
- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ 1990 የፀደቀ
- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ማናቸውንም ዓይነት መድልኦዎች ለማስወገድ ያወጣው ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ 1981 የፀደቀ

- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ቻርተር እ.ኤ.አ 1986 የፀደቀ
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የህፃናት መብቶችና ደህንነት ጥበቃ ቻርተር እ.ኤ.አ 1990 የፀደቀ
- የአፍርካ አንድነት ድርጅት የሰብዓዊና የህዝቦች መብቶች ቻርተር የሴቶች መብቶች ፕሮቶኮል በአፍርካ በ2003 እ.ኤ.አ የፀደቀ

እነዚህ ዓለም ዓቀፍ ሰነዶች ማናቸውንም አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ልማዳዊ አሰራሮች አጥበቀው ይቃወማሉ/ያወግዛሉ:: አባል ሃገሮችም ድርጊቶቹን እንዲያስወግዱ የህግ፣ የአስተዳደር፣ ሕብረተሰቡን የማስተማርና ሌሎችም መሰል እርምጃዎች እንዲወስዱ ግዴታን ይጥላሉ:: ትንሹን ግዴታ (core minimum obligation)

ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 7 “ማንም ሰው ጨካኝ ኢሰብዓዊና አዋራጅ በሆነ መንገድ መያዝ ወይም መስተናገድ አይገባውም::”

በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም ዓይነት መድልአዎች ለማስወገድ የወጣ ኮንቬንሽን አንቀፅ 2(ረ) እና 5(ሀ) “... በሴቶች ላይ አድለዕዊ አሰራርን የሚያንፀባርቁ ማናቸውንም ዓይነት ሕጎች፣ ደንቦች፣ ባህላዊ አሰራሮችና ልማዶችን ማስወገድ የአባል ሀገሮች ግዴታ ነው::

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የአፍሪካ የሴቶች መብት ፕሮቶኮል “በሴቶች ሰብዓዊ መብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸውን ድርጊቶች/እሴቶች የሚፃረሩ” ሲል ያስቀምጣቸዋል። ይህም ከመድልአዊ አስተሳሰብና ልማዳዊ አሰራር የመጣ ነው።

የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው ጥናታዊ ፅሑፍ በሴቶችና በህፃናት የሚደረጉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን ያሳያል። ጥናቱ እንዳመለከተው በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በሴቶች እና ህጻናት ላይ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች 140 ደርሰዋል። ይህ ቁጥር ከዛሬ 15 ዓመት በፊት እ.ኤ.አ. 1998 ዓ.ም 88 ብቻ ነበር። ይህ የሚያመለክተው ታዲያ በሴቶች እና በህፃናት ላይ እየተተገበሩ ያሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ቁጥር እና አይነት ስልጣኔ በተስፋፋበት በአሁኑ ወቅትም እያሻቀበ መምጣቱን ነው። በሚገርም ሁኔታ ደግሞ ከእነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል 90 በመቶዎቹ በሴቶች እና ህጻናት ላይ አሉታዊ፣ አካላዊ እና አእምሯዊ ተፅዕኖ መፍጠራቸው ነው። ይህም ከተለያየ ምክንያት እንደሚመነጭ የዘርፉ ሙሁራን ይናገራሉ።

ከነዚህ ምክንያቶች ዋነኛ የሆነው ምክንያት በስራ ላይ ያሉ ህጎች ወደ ሕብረተሰቡ ዘልቀው የሚፈለገው የአመለካከት ለውጥ ማምጣት አለመቻላቸው ነው(legal penetration)።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚባሉት ውስጥ ለምሳሌ የሴት ልጅ ግርዛት፣ እንጥል መቧጠጥ፣የወተት ጥርስን መንቀል፣ ጠለፋ እና ያለ እድሜ ጋብቻ፤ አካላዊ ቅጣት ወይም ጭካኔ የተሞላው እና ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ቅጣት በሕጻናት ላይ መፈፀም እና በወሊድ ዙርያ የሚፈፀሙ አካላዊ እና ስነ-አእምሮአዊ ጉዳቶች በሚለው ይዘረዘራሉ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የአሳሳቢነቱ ደረጃ እያሻቀበ የመጣው ያለ እድሜ ጋብቻ ነው ። በተለይ በገጠር የሀገሪቱ ክፍሎች ይህ ያለ እድሜ ጋብቻ በስፋት የሚተገበር መሆኑ በጥናት ተመልክ~ል። ለአብነት ያህልም በአማራ ክልል ያለው ያለ እድሜ ጋብቻ 44 ነጥብ 8 በመቶ ሲሆን፣ በትግራይ ክልል ደግሞ 34 ነጥብ 1 በመቶ ነው። ይህ ቁጥር በቤንሻንጉል ጉምዝ 31 ነጥብ 9 በመቶ ሲሆን፣ በመዲናችን አዲስ አበባም 32 ነጥብ 3 በመቶ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።(እ.ኤ.አ በ2011 በሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ይፋ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያመለክተው)

ያለ እድሜ ጋብቻ በቤተሰብ ፍቃድ እንዲሁም በጠለፋ የሚካሄድ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ቢሆንም፣ ጠለፋ በራሱ ደግሞ ሌላው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት እንደሆነ ተቀምጧል። ጠለፋም ልክ እንደሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሁሉ ከከተማ ይልቅ በገጠር የሀገሪቱ ክፍሎች በስፋት የሚዘወተር ተግባር ነው። ይህ ድርጊት በተለይ በደቡብ የሀገራችን ክፍል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶችን እየጎዳ መሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ ። ይህም 17 ነጥብ 5 በመቶ መሆኑ ተቀምጧል።

በመቀጠልም የሚገኘው የኦሮሚያ ክልል ሲሆን ይኸውም 11 ነጥብ 5 በመቶ ነው። ትግራይ ክልል በ5 ነጥብ 9 በመቶ እንዲሁም አማራ ክልል በ5 ነጥብ 5 በመቶ ተከታትለው ተቀምጠዋል። ከዚህ መመልከት የሚቻለው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ሕጎች ምን ያህል ወደ ገጠሩ ማሕበረሰብ ዘልቀው መግባት እንዳልቻሉ ነው።

1. የባህል ምንነትና ያለው ህገ-መንግስታዊ እውቅና

1.1 ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?

በመግቢያው ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ ባህል የአንድን ማሕበረሰብ ምንነትና ማንነት በተለያዩ የኑሮ ገፅታዎች የሚከወን ልማዳዊ ድርጊት ነው። ይህም በእምነቱ ፣ በkንkው፣ በአናዕናዕሩ፣ በአለባበሱ፣ በጋብቻው፣ በግጭት መፍቻ ዘዴው፣ በሰርግ አከባበር ወዘተ በመሳሰሉ ድርጊቶች የሚገለፁ ናቸው።

ያለፉት ስርዓቶች ለብዝሃነት ብዙ ደንታ ያልነበራቸው ቢሆኑም በተግባር ግን የባህል ብዝሃነት በሕብረተሰቡ ውስጥ እንደነበሩ እና ሕብረተሰቡንም ያስተዳድሩ እንደነበረ ይታወቃል (pragmatics nature of legal pluralism) ።

የአሁኑ መንግስት ደግሞ ፌዴራላዊ ስርዓትን በህገ-መንግስቱ እወቅና በመስጠት ለብዝሃነት መዳበር ጥሩ መደላድል ፈጥሮአል። በመሆኑም ዜጎች ባህላቸውን በነፃነት እንዲያፀባርቁ ረድ~ቸዋል።

በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39(2) እንዲህ በሚል ገልፆታል፡፡ “ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ፡ ብሔረሰብ፡ ሕዝብ በkንkው የመናገር፡ የመፃፍ፡ kንkውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለፅ፡ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የማሳደግ የመንከባከብ መብት አለው፡፡”

ከዚህ ባሻገር በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 91 ንኡስ 1 “መንግስት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን ፣ ዴሞክራሲንና ሕገ-መንግስቱን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና አንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡” ከዚህ ለመረዳት እንደሚቻለው ጠቃሚ ባሕሎች መንከባከብና ማሳደግ የመንግስትና የሕዝብ ኃላፊነት እንደሆነ ነው፡፡ ሆኖም ግን አንዳንድ ባህሎች፣ ወጎች እና ልማዳዊ አሰራሮች ከመሰረታዊ መብቶችና ሰብአዊ ክብርን ፤ ዴሞክራሲንና ሕገ መንግስቱን የማያከብሩና የሚጥሱ/የሚጣረሱ እወቅና የተነፈጋቸው እንደሆኑ ያሳያል፡፡

1.2.ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ምንድን ናቸው?

ሁሉም ልማዳዊ ድርጊቶች ጠቃሚ እንዳልሆኑም የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት የልማዳዊ ድርጊቶች የእውቅና ቀመር ያሳያል፡፡ ለምሳሌ ልማዳዊ አሰራር ከህገ-መንግስቱ እሴቶች ከተጋጨ ተፈፃሚነት እንደማይኖራቸው በአንቀፅ 9 ንኡስ 1 የህገ-መንግስት የበላይነት መርህ ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ደግሞ ማናቸውም የሕብረተሰቡ ልማዳዊ የሆነ አሰራር ሲሆኑ ውጤታቸው ደግሞ አሉታዊ ተፅዕኖ በተለይም በሴቶች እና

በሕፃናት መብት ላይ የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ወጎችና ልማዳዊ አሰራሮች እንደሆኑ የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 35 ንኡስ 4 ያመለክታል።

ከዚህ ባለፈ የሕገ መንግስቱን አንቀፅ 91 ንኡስ 1 የተደነገገው ኃይለ-ቃል የሚጥሱ ናቸው። በዚህም በአንቀፅ 9 ንኡስ 1 ተፈፃሚነት ሊኖራቸው እንደማይችሉ በግልፅ ደንግጓል።

ሰብዓዊ መብቶችን የሚጥሱ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ጨምሮ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በምዕራፍ 3(የሰብዓዊ መብቶች ምዕራፍ) ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው። (በአንቀፅ 13 ንኡስ 1 የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት ያስቀምጣል። በተመሳሳይ አንቀፅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግስትም አዋጅ ቁጥር 59/1994 ዓ.ም ተመሳሳይ ሃሳብ ደንግጓል።)

1.3.ህገ-መንግስታዊ ክልከላና እውቅና

የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ልማዳዊ ድርጊቶችን በሁለት ከፍሎ ያያቸዋል። እነዚህም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጠቃሚ ልማዳዊ አሰራሮች መሆናቸውን ከተለያዩ የህገ-መንግስቱ አንቀፆች መመልከት ይቻላል። ይህም ደግሞ ህገ-መንግስቱ የበላይ የህግ አካል በመሆኑ መከበርና መፈፀም እንዳለበት **የህጎች ተዋረድ ያሳያል**።

ከዚህ በመነሳት ልማዳዊ ድርጊቶች ሁለት ገፅታዎች እንዳላቸው መገንዘብ ጠቃሚ ነው፡፡ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች መሆናቸውን፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ህገ-መንግስት አዋጅ ቁጥር 59/1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣውም በአንቀፅ 112 ንኡስ 1 "የክልሉ መንግስት መሰረታዊ መብቶችና ሰብአዊ ክብርን እንዲሁም ዴሞክራሲንና ሕገ-መንግስትን የማይቃረኑ ባህሎች ና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡"

2. <u>የህፃናት ጥበቃና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች</u>

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ጾታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው፡፡ (አንቀፅ 215 የፌዴራል መንግስት የቤተሰብ ሕግና የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 226፡፡)

ህፃናት በአእምሮአቸው፣ በአካላቸውና በስነ- ልቦናቸው ያልበሰሉ፣ የማመዛዘንና ተገቢና ጠቃሚ የሆነ ውሳኔ የማስተላለፍ አቅም (mental competence) የሌላቸው የሕብረተሰብ አካል ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ለተለያዩ ነገሮች በቀላሉ ተጋላጭ የመሆን ዕድላቸው የሰፋ ነው፡፡ ይህንን ተጋላጭነታቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ መብቶችና ከለላዎች ከሌሎች ሰዎች ያላቸው መብቶች በተጨማሪ መስጠት አስፈላጊና አስገዳጅ ሁና፟ል፡፡

ይህንን የተጋላጭነታቸው ወሰን ግምት ውስጥ በማስገባት የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት በተለያዩ አንቀፆች ለህፃናት ጥበቃ አድርገዕል። በተለይም በአንቀፅ 36 ንኡስ 2 እንዲህ ደንጊገዕል። ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተkሞች ፣ በፍርድ ቤቶች ፣ የአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።

ሁሉም ሕፃናት ተጋላጭ ቢሆኑም ሴቶች ሕፃናት ግን የበለጠ የተጋላጭነት ደረጃቸው ይጨምራል ። ሴት በመሆናቸው ብቻ በሕብረተሰቡ የሚያጋጥማቸው አድልአዊ አሰራር በርካታ ናቸው። በዚህም ልዩ ጥበቃ እንድደረግላቸው የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 35 ደንግገዕል።

- **አንድ ሕፃን ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የሚወጣበት (የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 322፣ 323 ፣324 እና 325)**
  - 14 ዓመት ሲሞላው
  - በአንቀፅ 18 ንኡስ 2 ጋብቻ የፈፀመ እንደሆነ (በከባድ ምክንያት ከ 18 ዓመት ዕድሜ በታች በፍትሕ ቢሮው ፈቃጅነት ያገባ እንደሆነ)

ሆኖም እነዚህን ውሳኔዎች ሲሰጡ የልጁን ጥቅም እና ደህንነት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

ከዚህ በተጨማሪ በአንቀፅ 34 ንኡስ 2 ላይ ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመስረት እንዳለበትና በህግ የተደነገገው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች ብቻ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እነዚህን ክልከላዎች እና እሴቶች የሚጣረሱ ልማዳዊ አሰራሮች ናቸው።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግስትም አዋጅ ቁጥር 59/1994 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣውም በተመሳሳይ ለሴቶችና ለሕጻናት ካላቸው ተጋላጭነት በመነሳት ልዩ ጥበቃ አድርገዋል። **ለምሳሌ በአንቀፅ 34 ንኡስ 1 ፣ 2 እና 3፣ 35 ንኡስ 1 እና 4፣ 36 ወዘተ**

2.1. ህፃናት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ

2.1.1. ጋብቻ ለመፈፀም መማላት ያለባቸው ሁኔታዎች

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995 በአንቀፅ 1 ቅደመ-ጋብቻ መተጫጨት አስገብ~ል። ይህም እንደ አንደ የክልሉ እሴት በማየት ለዘላቂ ጋብቻ ጠቃሚ ነው የሚሉ አሉ። ምክንያቱም ተጋቢዎች ለመጠናናት ጊዜና ዕድሉ ይኖራቸዋል የሚል ነው። ከዚህ ባለፈ ተጋቢዎች የስነ-ልቦ ዝግጅት እና የገንዘብ ወጭአቸውን ለመወሰን በቂ ጊዜ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። ሆኖም የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህጎች ግን መተጫጨት የሕጻናት መብቶችን ለመሸርሸር እና ለመጣስ በር የሚከፍት አደገኛ አካሄድ ነው ብለው ያስቀምጡታል።

- ትጭጭት ለአካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለወደፊት ትዳር እንደሚመሰርቱ በይፋ ገልፀውና የጋብቻ መፈፀሚያ ቀን ቆርጠው በመስማማት የእጮኛውና የእጮኛይቱ ቤተዘመዶች ተወካዮችና ምስክሮቻቸው በታዛቢነት በተገኙበት ሥነ-ስርዓት ፈቅደው የሚለዋወጡት የርስ በርስ ቃል ኪዳን ነው::

ሴቶች **በነፃ ፍቃዳቸው** የመሰረቱት ጋብቻ **ለህይወታቸው፡ ለክብራቸው እና ለእኩልነታቸው ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው::**

18 ዓመት ዕድሜ ዝቅተኛው የጋብቻ ዕድሜ እንደሆነ በተለያዩ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው አለም አቀፍ ህጎችና የፌዴራል የቤተሰብ ህግና የአብክመ የቤተሰብ ሕጎች ይደነግጋሉ:: ይህ የጋብቻ ዕድሜ በሁለት ዓመት ዝቅ የሚልበት ሁኔታዎች አሉ:: ለምሳሌ **ከባድ ምክንያት** ሲያጋጥም የፌዴራሉ ፍትሕ ሚኒስቴር እና የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ካመነበት በሁለት ዓመት ዝቅ አድርጎ ተጋቢዎችን እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል::

ይህ ድንጋጌ ቢኖርም ዕድሜን ማረጋገጥ አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም **የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 760/2012** በቅርቡ የወጣና ለማስፈፀም የሕብረተሰቡ ግንዛቤ መፈጠር ያለበት ነው:: ማለትም የልደት ፣ የሞት ፣የጋብቻ፣ የአባትነት ማረጋገጥ እና ጉዲፈቻነት ናቸው ሁኔታዎች መመዝገብ እንዳለባቸው ያስቀምጣል::

ጋብቻ በትርጉሙ አካለ መጠን የደረሱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለዘሌቀታው አብሮ በመኖር ሃሳብ በራሳቸው ነፃ ምርጫ በሕግ ለመዋሐድ ፈቅደው በይፋ የሚመሰርቱት ግንኙነት ወይም በዚሁ ግንኙነታቸው አማካኝነት የሚዋቀር ሕጋዊ ተkም ነው::(የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 11)

2.1.2 የሚከተሉትን ነጥቦች ለጋብቻ መፈፀም ቅደመ-ሁኔታዎች ናቸው::

- የተጋቢዎች ለመጋባት ነፃ እና ሙሉ ፍቃድ
- ሁለቱም ተጋቢዎች ከ18 ዓመት ዕድሜ በላይ መሆን አለባቸው
- የሥጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና አለመኖሩን መረጋገጥ አለበት
- በጋብቻ ላይ ጋብቻ የማይቻል ስለመሆኑ

2.1.3. የጋብቻ ቅድመ-ሁኔታዎች መፃደል ውጤት

- በኃይል ወይም በስህተት በተገኘ ፍቃድ የተመሰረተ ጋብቻ በህግ ፊት አይፀናም::(የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 24 እና 25)

- ጋብቻ እንዳይፈፀም ሰለመቃወም(የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 29)
- በጋብቻ ቅድመ ሁኔታዎች መፅደል ጋብቻ እንዳይፈፀም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል።

በመሆኑም በእድሜ መፅደል ምክንያት የተገኘ ጋብቻ ወላጆች ፣አቃቤ ህግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው ጋብቻውን መቃወም ይችላል። ከዚህ ለመገንዘብ የሚቻለው በእድሜ መፅደል ምክንያት መቃወሚያ የሚያቀርቡ አካላት ያለ ገደብ የተጠቀሱ ናቸው። ይህም የሕጻናት መብት ከማስጠበቅ አኳያና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ከማስቀረት የራሱ ጥሩ አስተዋፅኦ አለው። ያለ ዕድሜ ጋብቻ ከመከላከል አንፃርም የራሱ በጎ ጎን አለው።

<u>ያለ ዕድሜ ጋብቻ በህፃናት ላይ የሚያስከትለው ውጤት</u>

- በትምህርታቸው፡- ያkርጣሉ ውጤታማ አይሆኑም
- በጤንነታቸው(በአካላቸው ፣ በስነ አእምሮአቸው፣ በህይወታቸው)- ፌስቱላ ፣ በወሊድ የሚያጋጥም የሞት አደጋ
- ከህብረተሰባዊ ተሳትፎ መገለልን(social stigma and absence of participation)

- ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት(በሕፃንነታቸው መውለድ ከጀመሩ ላልጠመጠነ የቤተሰብ ኑሮ ይዳርጋቸዋል።)
- በሰብዓዊ ክብራቸው የመዋረድ እና የበታችነት ስሜት ያሳድርባቸዋል።

2.2.ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ እይታ

2.2.1. በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ስለ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ያለው ክልከላ

የድሮው የወንጀለኛ መቀጫ ሕግ በአዲሱ የወንጀል ሕግ መተካቱ ወይም መሻሻሉ ምክንያቶች በመግቢያው ላይ እንደተቀመጠው ፡-

- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሕፃናትና በሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ሥቃይ የሚያስከትሉ መሆኑን የወንጀለኛ መቀጫ ሕጉ እውቅና አለመስጠቱ ነው።
- ለውጦች (የሃይማኖት፣ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የህዝቦች እኩልነት ፣ የዜጎችና የነዋሪዎች ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች፣ እንዲሁም ሰብዓዊ መብቶች ፣ ይልቁንም እንደ ሕፃናትና ሴቶች የመሳሰሉ የህበረተሰቡ ክፍሎች መብቶች ፣ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና

በህገ-መንግሰቱ ዕውቅና ማገኘታቸውን ተከትሎ)=social transformation(social engineering theory)

- አንቀጽ 561 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴትና ሕፃናት ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ(በገንዘብ ወይም ከ3 ወር እስከ 1 ዓመት ቀላል እስራት)
- አንቀጽ 562 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴትና ወይንም በሕፃናት አካል ላይ ጉዳት ማድረስ(በገንዘብ ወይም 6 ወር ባልበለጠ ቀላል እስራት)
- አንቀጽ 564 በትዳር ገፅኛ ወይም ከጋብቻ ውጭ በሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚኖር ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ
- አንቀጽ 565 ሴትን መግረዝ(5 መቶ ብር ባላነሰ የገንዘን ቅጣትና ከ3 ወር ባላነሰ ቀላል እስራት)
- አንቀጽ 566 **የሴት ብልትን መስፋት**(ከ3 እስከ 5 ዓመት እስራት)
- አንቀጽ 567 **በሌሎች ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት የሚፈፀም የአካል ጉዳት** (ከ6 ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት)
- አንቀጽ 568 **በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፍ**(ከ3 እስከ 5 ዓመት እስራት)

- አንቀጽ 569 **በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ ስለመሆን (5** መቶ ብር ባልበለጠ የገንዘን ቅጣትና ከ3 ወር ባላነሰ ቀላል እስራት)

- አንቀጽ 570 **ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች እንዳይፈፀሙ ማነሳሳት (5 መቶ ብር ባላነሰ የገንዘብ ቅጣትና 3 ወር ባላነሰ ቀላል እስራት)**

በቤተዘመድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

❖ በጋብቻ ስርዓት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

- አንቀፅ 646 ጋብቻ በተንኮል ወይም በማታለል መፈፀም(ከሁለት ዓመት ወይም ከአምስት ሺ ብር የማይበልጥ)

- አንቀፅ 647 በሕግ የተከለከለ ጋብቻን ማስፈፀም እና ምስክር የሆነ ወይም መፈፀም (ከሦስት ዓመት ያልበለጠ እስራት ወይም ከአምስት ሺ ብር የማይበልጥ መቀጮ)

❖አንቀፅ 648 ያለ ዕድሜ ጋብቻ

- ተበዳይዋ ከ13 ዓመት በላይ ከሆነች ከ3 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት

- ተበዳይዋ ከ 13 ዓመት በታች ከሆነች ከ7 ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት

3. <u>የማሕበረሰቡ ግዴታዎችና ተጠያቂነት</u>

በኢፌዴሪ ሕገ- መንግስት አንቀፅ 16 የሰዎችን የአካል ደህንነት የመጠበቅ መብት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር በኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ የተካተቱ ወንጀሎች፡፡ በመሆኑም

ማሕበረሰቡ የድርጊቱ ባለቤትና ተጎጂ በመሆኑ የተጣለበትን ግዴታና መብት አወቆ እንዲሰራ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም በአብክመ የቤተሰብ ሕግና ሕገ-መንግስት ቤተሰብ የህብረተሰብ ተፈጥሮአዊ መነሻ በመሆኑና **በሕብረተሰቡና በመንግስት ያላሰለስ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን ስለ ሚገልፅ፡፡**

በተለይ **የሃይማኖት አባቶች፣ የቀበሌ አመራሮች እና የሀገር ሽማግሌዎች ያላቸውን ተሰሚነት ተጠቅመው** ሕብረተሰቡን በማስተማርና በመምከር ከጉዳት መከላከልና መጠበቅ አለባቸው፡፡

ይህም የማሕበረሰቡ ክብርና ደህንነት የሚሰጠው ዋጋ ለማምጣት አንዱ ጥረት በመሆኑ ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ ሲያስተላልፉ **የህፃናት ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት የሚለው ሕገ-መንግስታዊ መርህ ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡**

4. የመንግስት ግዴታችና ተጠያቂነት

በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት በምዕራፍ 3(የሰብዓዊ መብቶች ምዕራፍ) የተቀመጡትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

የክልሉ መንግስት መሰረታዊ መብቶችና ሰብዓዊ ክብርን እንዲሁም ዴሞክራሲንና ሕገ-መንግስትን የማይቃረኑ ባህሎች ና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ ባሻገር ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት መንግስት ሕብረተሰብ አቀፍ የሆነ የንቃተ -ህሊና የንቃተ-ህሊና ስራ መስራት አለበት፡፡

መንግስት በተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙርያ የሚሰሩ እና ይህንን ለማስቀረት የሚተጉ ወገኖች መደገፍና ማበረታት አለበት፡፡

መንግስት የተለያዩ ብዙሃን መገናኛዎችን በመጠቀም ለሕብረተሰቡ ስለ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስከፊነት ግንዛቤ መስጠት አለበት፡፡

5. ዋቢ መፅሐፍቶች

1. ፕሮፌሰር ጥላሁን ተሾመ.(1997 ዓ.ም). ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢትዮጵያ ሕግጋት እይታ፡ ከዩኒሴፍ በተገኘ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማሕበር የተዘጋጀ.
2. Dawit Assefa et al. (2005). Harmful Traditional Practices for the Ethiopian Health Center Team.
3. Rita Mutyaba. (2011). Early Marriage: A Violation of Girls' Fundamental Human Rights in Africa. The *International Journal of Children's Rights. Vol. 19, Martinus Nijhoff publishing*
4. Jo Boyden et al (2012). Harmful Traditional Practices and Child Protection: Contested Understandings and Customs of Female Early Marriage and Genital Cutting in Ethiopia. Available at http://www.tandfonline.com/toc/cdip20/current
5. Berihun M. Mekonnen and Harald Aspen. (2009). Early Marriage and the Campaign against It in Ethiopia.

ሕጎች

- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብልክ ሕገ መንግስት ቁጥር 1/1987 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብልክ የወንጀል ሕግ አዋጅ ቁጥር 414/1996
- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብልክ የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ እና ብሔራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2012
- የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992
- የአብክመ ሕገ መንግስት 59/1994
- የአብክመ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 79/1995
  - ኢትዮጵያ ፈርማ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሕጎች